**ይህ ሰነድ ለህትመት አገልግሎት ብቻ የታሰበ ነው። ዋናው ቅጽ https://doe.virginia.gov/ParentInvolvementSurvey ላይ ይገኛል።**

# Virginia Department of Education (የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ) የ 2026 የወላጆች ተሳትፎ የዳሰሳ ጥናት

በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን፣ የቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ "የትምህርት ቤቶች የወላጆችን ተሳትፎ ማመቻቸት ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ውጤቶችን ለማሻሻል ያለውን ፋይዳ" ለዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት። **በቨርጂኒያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በግለሰባዊ የትምህርት መርሃግብሮች (IEPs) አማካኝነት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን የሚያገኙ ተማሪዎች ቤተሰቦች በሙሉ ይህንን አጭር የዳሰሳ ጥናት እንዲያጠናቅቁ ይጠየቃሉ።** VDOE የዚህ ጥናት ውጤቶችን በመጠቀም በልዩ ትምህርት ሂደት ውስጥ የወላጆች ተሳትፎን ለማሻሻል እና በኮመንዌልዝ ውስጥ ላሉት ተማሪዎች ሁሉ ውጤቶችን ለማሻሻል ይረዳል። የሚሰጡት ምላሾች ማንነታቸው ሳይታወቁ የሚመዘገቡ መሆናቸውን እና ከልጅዎ ጋር በቀጥታ ሊያያዙ እንደማይችሉ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

በቨርጂኒያ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በ IEPs አማካኝነት የልዩ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙ ከአንድ በላይ ልጆች ያሉዋቸው ወላጆች ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ የዳሰሳ ጥናት አጠናቀው ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ለብዙ ልጆች ጥናቱን የሚወስዱ ከሆነ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ የተለየ ብራውዘር (Safari፣ Google፣ ወዘተ) ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ (ላፕቶፕ፣ ሞባይል ስልክ፣ አይፓድ፣ ወዘተ) መጠቀም እንደሚኖርብዎት እባክዎ ልብ ይበሉ።

ይህንን የዳሰሳ ጥናት በሚሞሉበት ጊዜ፣ ባለፈው የትምህርት ዘመን የነበረዎትን ልምድ እንዲገመግሙ ታስበው ለተዘጋጁ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣሉ። ስለዚህ የዳሰሳ ጥናት ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት፣ እባክዎ የ VDOE የቤተሰብ ተሳትፎ ባለሙያ/የልዩ ፕሮጀክቶች አስተባባሪ የሆኑትን ዶ/ር Chiquita Seaborne በስልክ ቁጥር (804) 418-4672 ወይም በኢሜይል Chiquita.Seaborne@doe.virginia.gov ያግኙ።

እባክዎ የተጠናቀቀውን የዳሰሳ ጥናትዎን ወደ እሚከተለው አድራሻ ይላኩ፦

ATTN: Survey Coordinator 20th Floor
Department of Special Populations
Virginia Department of Education
P.O. Box 2120
Richmond, VA 23218

# የ ስነ-ሕዝብ አወቃቀር ጥያቄዎች

ለሚከተሉት የስነ-ሕዝብ አወቃቀር ጥያቄዎች መልስ ይስጡ፡-

1. *ባለፈው* የትምህርት ዓመት ልጅዎ የትኛው የትምህርት ክፍል ውስጥ ተምሯል?

2. *ባለፈው* የትምህርት ዓመት የልጅዎ ዕድሜ ስንት ነበር?

3. ባለፈው የትምህርት ዓመት የልጅዎ የትምህርት ደረጃ ስንት ነበር? (ቅድመ-መደበኛ፣ አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ፣ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት)

4. *ባለፈው* የትምህርት ዓመት የልጅዎ ዋና የትምህርት እክል ምን ነበር?

5. የልጅዎ ዘር/ብሔር ምንድን ነው?

## የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች የእርስዎን ምላሽ በተሻለ ሁኔታ የሚገልጽ አንድ ምርጫ ላይ ያክብቡ፦

6. የልጄ ትምህርት ቤት ለአካል ጉዳተኛ ልጄ የሚሰጡ አገልግሎቶችን እና ውጤቶችን ለማሻሻል እንድሳተፍ ረድቶኛል።

   እስማማለሁ          አልስማማም

7. ጥያቄዎችን ለመጠየቅ፣ ስለ ልጄ የትምህርት እድገት ለመወያየት፣ እንዲሁም ስለ ልጄ የልዩ ትምህርት ፕሮግራም እና አገልግሎቶች ያሉኝን ስጋቶች ለመግለጽ ነፃነት ይሰማኝ ነበር።

   እስማማለሁ          አልስማማም

8. የልጄ ትምህርት ቤት እና እኔ በትምህርት ዓመቱ በሙሉ "የመልዕክት ምልልስ ያለበት" ግንኙነት ነበረን።

   እስማማለሁ          አልስማማም

9. ስለ ትምህርት ቤት እና ማኅበረሰብ ሀብቶች፣ ድጋፎች፣ አገልግሎቶች፣ እና ስለ ልዩ ትምህርት ሂደት መረጃ እና እርዳታ ለማግኘት የምገናኛቸው የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች መረጃ ተሰጥቶኛል።

   እስማማለሁ          አልስማማም

10. ለልጄ ስላሉት የአገልግሎት እና የትምህርት ቦታ አማራጮች መረጃ ተሰጥቶኛል እንዲሁም በልዩ ትምህርት ስብሰባዎች ወቅት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ዕድል ተሰጥቶኛል።

   እስማማለሁ          አልስማማም

11. እባክዎ ተጨማሪ አስተያየት ካለዎት ይህንን ቦታ ይጠቀሙ።

12. በ VDOE ውስጥ ያለ አንድ ሰው በዚህ የዳሰሳ ጥናት ውስጥ ስላሉት ጥያቄዎች ወይም ስለ ልዩ ትምህርት ሂደቱ ስላሉብዎት ሌሎች ስጋቶች እንዲያነጋግርዎት ይፈልጋሉ? እባክዎ መልስዎ ላይ ያክብቡ።

   አዎ          አይደለም

13. ለጥያቄ #12 መልስዎ "አዎ" ከሆነ፣ እባክዎ የሚከተሉትን የእውቂያ መረጃዎች ይስጡ፦

ስም፦

ኢሜይል፦

አድራሻ፦

ስልክ ቁጥር፦

## ተጨማሪ መረጃ

ስለ ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ስለዚህ ጥናት ከአንድ አካል ጋር መነጋገር ከፈለጉ፣ የVDOE የልዩ ትምህርት የወላጅ እንባ ጠባቂን ማግኘት ይችላሉ። እንባ ጠባቂው ፍትሐዊ የሥራ ሂደት እንዲኖር የሚሚገት፣ እንዲሁም ለወላጆች፣ ለአሳዳጊዎች፣ ለተሟጋቾች፣ ለአስተማሪዎች እና የአካል ጉዳት ላለባቸው ተማሪዎች ምስጢራዊና መደበኛ ያልሆነ እርዳታ እና ድጋፍ የሚሰጥ ገለልተኛ አካል ሆኖ ያገለግላል። የልዩ ትምህርት የወላጅ እንባ ጠባቂው ህጋዊ ባልሆኑ የልዩ ትምህርት ጉዳዮች ላይ ለወላጆች እንደ መረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። ተጨማሪ መረጃ የወላጅ እንባ ጠባቂ ኃላፊነቶች በ VDOE ድህረ ገጽ፣ https://www.doe.virginia.gov/programs-services/special-education/resolvingdisputes/parent-ombudsman-for-special-education ላይ ማግኘት ይቻላል። የወላጅ እንባ ጠባቂን በስልክ ቁጥር (800) 422-2083 ወይም በኢሜይል specialeducationombudsman@doe.virginia.gov ማግኘት ይቻላል።

የቤተሰብ ተሳትፎ ማእከል (CFI) ሌላው ለወላጆች የሚቀርብ መገልገያ ነው። Center for Family Involvement (የቤተሰብ ተሳትፎ ማእከል) ቤተሰቦች፣ ልጆች እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ወጣቶች የሚፈልጉትን ሕይወት እንዲመሩ ለማስቻል ቤተሰቦች እንደ ተሟጋች፣ አማካሪ እና መሪ ያላቸውን ክህሎት ለማሳደግ አብሮ ይሠራል። ስለ CFI ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የCFI ድህረ ገጽን በwww.centerforfamilyinvolvement.org መጎብኘት ይችላሉ። CFIን በስልክ ቁጥር (877) 567-1122፣ ወይም በኢሜይል cfihelpline@vcu.edu ማግኘት ይቻላል።

ስለ ወላጆች ስልጠና እድሎች ወይም ስለ ወላጅ ድጋፍ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የወላጅ ትምህርታዊ ድጋፍ ሰጪነት እና ስልጠና ማዕከል (PEATC) ድህረ ገጽን www.peatc.org ይጎብኙ ወይም በ(800) 869-6782 ይደውሉ። እንዲሁም PEATC ን በኢሜይል partners@peatc.org ማግኘት ይችላሉ።